# ከዳቦ ናፋቂ ህዝብ የተመነተፈ ገንዘብ ለሽብር?

ቶሎሳ ኡርጌሳ

Utolosa@yahoo.com

ሰሞኑን ለንባብ የበቃው ሰንደቅ የተሰኘው ሀገር በቀል ጋዜጣ "የሻዕቢያ መንግስት በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ የዘረጋውን የትርምስ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አጠናክሮ ቀጥሏል" የሚል ዘገባ አስነብቦናል። ለዚህም በማሳያነት የገዛ ራሱን ህዝብ በረሃብ አለንጋ በመግረፍ ላይ የሚገኘው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን በማተራመስ አቋሙ ፀንቶ፤ ራሱን "የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር" (ኦብነግ) እያለ የሚጠራውን የግብረ-ሽበራ ቡድን ጉባኤውን አስመራ ውሰጥ እንዲያካሂድ ሙሉ ድጋፍ መስጠቱን አውስቷል።

እርግጥ የሻዕቢያን ተፈጥሮአዊ ባህሪንና የአቶ ኢሳያስን ጦር አምላኪነት የሚያውቅ ማንኛውም ሰው 'ተግባሩ የኤርትራ መንግስት የተለመደ ሽብር ናፋቂነት በመሆኑ አዲሱ ነገር ምንድር ነው?' ማለቱ የሚቀር ይመስለኝም። አዎ! አባባሉ ትክክል ነው። ግና አዲሱ ነገር የኤርትራ መንግስት ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአምባሳደር አርዓያ ደስታ አማካኝነት "ሀገሬ ከአሸባሪዎች ጋር ግንኙነት የላትም" ካለ አንድ ወር እንኳን ሳይሞላው፤ በግብፅ የቀድሞ መንግስታት ተጠፍጥፎ እንደተሰራ ከሚነገርለት ከአሸባሪው ኦብነግ ጋር የተላላኪነት ጋብቻውን አጠናክሮ መቀጠሉና በዚህም አንድ ሐሙስ የቀረው ሻዕቢያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው በውሸት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለዓለም ይበልጥ እያረጋገጠ መምጣቱን ነው።

እናም በዛሬው ፅሑፌ በሻዕቢያ ተላላኪነት የሚተዳደረው አሸባሪው "ኦብነግ" ማነው?፣ የአስመራው ቡድን ኑሮ እንደ መርግ የከበደውን የሀገሩን ህዝብ ከረሃብ ከማውጣት ይልቅ የህዝቡን ገንዘብ እየመነተፈ ለምን ለአሸባሪዎች ይረጫል?፣ የኤርትራ መንግስት ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት አዳራሽ ውስጥ እየተንጎማለለ "በአሸባሪነት ጉዳይ ከደሙ ንፁህ ነኝ" ባለ ማግስት እንደ ህፃን ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለምን መልሶ ይዋሽዋል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ለአንባቢዎቼ የተነሳሁበትን ርዕሰ ጉዳይ ለማስጨበጥ እሞክራለሁ። ይህም የኤርትራ መንግስት ከአሸባሪዎች ጋር ያለው የማይፋታ የካቶሊክ ጋብቻ የፀና እና መቼም ሊተወው የማይችለው መሆኑን ዓለም አቀፉ ማህበሰብም ይሁን ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንዲገነዘበው ያደርጋል ባይ ነኝ።…

## የአሸባሪው "ኦብነግ" ማንነት ሲጨረፍ

እንደሚታወቀው የአስመራው ሰውዬ ሀገራችንን ለማተራመስና ተበታትና ለማየት ካላቸው ፅኑ ፍላጐት በመነሳት ካከረፋ ፀረ-ሠላምና ፀረ-ህዝብ ጠባብና ትምክህተኛ ኃይሎች ጀምሮ እስከ ሰራ ፍለጋ ከሀገር እስከወጣ ዜጋ ድረስ ማደራጀትንና ማስታጠቅን ዋነኛው የመንግስታቸው

የድርጊት መርሀ-ግብር አካል አድርገውት ዛሬ ላይ ደርሰዋል፡፡…ለዚህ እኩይ ተግባራቸውም በኢፌዴሪ መንግስት በአሸባሪነት የተሰየሙትን የሀገር ውስጥና የውጭ ቡድኖችን በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ "ትልቁ ለማኝ ለትንሹ ለማኝ ይሰጣል" በሚል ቀመር በተላላኪነት ያገኙትን ዶላሮች ቃርሚያ እየሰጡ ተጠቅመውባቸዋል፤ እየተጠቀሙባቸውም ይገኛሉ። በመሆኑም ራሳቸውን "ኦነግ"፣ "ኦብነግ"፣ "ግንቦት ሰባት"፣ "አል-ሸባብ" እና "አል-ቃዒዳ" እያሉ የሚጠሩ ሽብርተኞች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሀገራችንን እንዲያሸብሩ በመላክ ያልቆፈሩት ድንጋይ አለ ለማለት አይቻልም፡፡

ከእነዚህ አሸባሪዎች ውስጥ ሰሞኑን ለአስመራው የጉባኤ ድግስ የተጠራው፣ በፀረ-ህዝብ ባህሪው በኦጋዴን ህዝብ የተተፋውና በሀገራችን መከላከያ ሰራዊት ድባቅ ተመትቶ በአሁኑ ወቅት ትርጉም የሌለው ደረጃ ላይ የደረሰው ራሱን "አብነግ" እያለ የሚጠራው ቡድን አንዱ ነው። አንዳንድ ፀሐፍት እንደሚያስረዱት ይህ የሽብር ቡድን ሀገራችን ሁሌም ሰላም እንዳይኖራትና የዓባይ ግድብን እንዳትገነባ በቀደምት የግብፅ መንግስታት የተቋቋመ ነው።

ከዚያም በኋላ ቢሆን የሽብር ቡድኑ ከኤርትራ መንግስት ከፍተኛ ድጋፍ በማግኘት በሀገራችንና በህዝባችን ደህንነት ላይ ያነጣጠሩ በርካታ የሽብር ጥቃቶችን ፈፅሟል፡፡ ይህ የሽብር ኃይል ከሽግግር መንግስቱ አፈንግጦ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሻዕቢያው አስተዳደርና በአል-ሸባብ ድጋፍ ብሎም የቅርብ ክትትል፤ በንፁሐን ሰዎች፣ በልማት ተቋማትና፣ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ንብረቶች ላይ ያነጣጠሩ የአሸባሪነት ተግባራትን ፈጽሟል፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከ1988 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ከ132 በላይ ሰዎች እንዲሞቱና ከ54 በላይ ደግሞ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስባቸው አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከ25 በላይ ሰዎችን አፍኖ ወስዷል፡፡

አሸባሪው "ኦብነግ" በተለያዩ ጊዜያት ሽብር ፈፃሚ ሰዎችን ኤርትራ ውስጥ አሰልጥኖና አስታጥቆ ወደ ሀገራችን እንዲገቡ ብሎም የሽብር ጥቃት እንዲያደርጉ ትእዛዝ ሲሰጥና ሲያስፈጽም መቆየቱ የሚታወስ ነው—የተላላኪ ተላላኪ ሆኖ። በዚህም የኢሳያስ አፈወርቂ ተላላኪ በመሆን በግንባር ቀደምትነት የግብረ-ሽበራ ሎሌ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝና የሻዕቢያ ቅጥረኛ ቡድን ሆኖ የሚንቀሳቀስ ጥቂት ኃይል ነው፡፡

ይሁንና እርሱም ሆነ ላኪው ሻዕቢያ በኦጋዴን በኩል ያደረጉት የሽብር ተግባር አልቀናቸውም። ምክንያቱም የሽብር ቡድኑ በአሁኑ ወቅት በሶማሌ ክልል ህዝብ "በተለይም ለነፃነቱ ነው የምታገለው" በሚለው የኦጋዴን ህዝብ ይሁንታ በማጣቱና በኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት በደረሰበት ተደጋጋሚ ወታደራዊ ኪሳራ ኃይል የለሽ ደረጃ ላይ የሚገኝ የጥቂት ግለሰቦች ስብስብ የሆነበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ ነው። ከዚህ ጎን ለጎንም በተለያዩ ጊዜያት አብዛኛው አባሉ

የሽብር ቡድኑን እኩይ ሴራ በመገንዘብ ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ተቀብለው ሀገር ውስጥ ሰላማዊ ህይወታቸውን በመምራት ላይ መገኘታቸው ቡድኑን ትርጉም የለሽ እንዲሆን ያደረገው ምክንያት ነው።

በአሁኑ ወቅትም ቢሆን 'የኢፌዴሪን ህገ-መንግስት በመቀበል ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ቀጥተኛ ድርድር ማድረግ አለብን' በሚሉ አባሎቹ እየተናጠ ያለው የተመናመነው የአስመራው "ኦብነግ"፣ በሞት አፋፍ ላይ ቆሞ በጣር ላይ እንዳለ በሽተኛ የሚመሰል ነው። ዳሩ ግን አቶ ኢሳያስ እንደ "ኦብነግ" ዓይነት ተላላኪዎች የሀገራችንን ሰላም ለማወክ አስፈላጊዎች ስለሚመስሏቸው ቡድኑን "እባክህን ጥለኸኝ አትሂድ" የሚል ጉባኤ አዘጋጅተው ሞቱን በገንዘብ ሃይል ለመግዛት ደፋ ቀና እያሉ ናቸው። ይሁንና የሻዕቢያው ጉባኤ የሽብር ቡድኑን 'ህገ-መንግስቱን እንቀበል' ሃሳብ ብዙም የሚቀይረው እንዳልሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ይስማሙበታል። ያም ሆነ ይህ ግን በእኔ እምነት ሻዕቢያ ይህን የመጨረሻ የቀቢፀ-ተስፋ ህልሙን በሽብር ቡድኑ አማካኝነት ለማስፈፀም ዳቦ ናፋቂ ከሆነው የኤርትራ ህዝብ ካዝና መንትፎ ገንዘቡን ባልሆነ ቦታ ከመበተን ውጪ ምንም ዓይነት ፖለካዊ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም።

## ከዳቦ ናፋቂ ህዝብ የተመነተፈ ገንዘብ ለሽብር?

የኤርትራ ኢኮኖሚ የቁልቁለት ጉዞውን ከተያያዘ ዓመታት ተቆጥረዋል። በዚህም ሳቢያ ህዝቡ የዕለት ጉርሱን ለማግኘት በሻዕቢያ ህብረት ሱቆች ደጃፍ እየተሰለፈ ዳቦ ናፋቂ ሊሆን ችሏል። የአቶ ኢሳያስ አገዛዝ ሁሉንም የኢኖሚ ዘርፎች በዕዝ ምጣኔ-ሀብት አሰራር በመያዙ በነፃነት የመገበያየት ነገር በዚያች ትንሽ ሀገር ውስጥ አይታሰብም። በተለይም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ጠቅልለው ይዘዋል በሚባሉትና በቅፅል ስማቸው "ክሻ" እየተባሉ የሚጠሩት አቶ ሃጎስ ገ/ሂወት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እየተቆጣጠሩ የህዝቡን ካዝና በማራቆት ለግብረ-ሽበራ ተግባር እንዲውል ያደርጋሉ።

ቀደም ባሉት ጊዜያት በአሜሪካ የኤርትራ አምባሳደር የነበሩት ሃጎስ (ኪሻ) ቅጽል ስሙ የተሰጣቸው ከገንዘብ ጋር ባላቸው የዘረፋ ንክኪ አማካኝነት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ግለሰቡ የአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ "የገንዘብ ቦርሳ" እየተባሉ የሚጠሩ ሲሆኑ፣ ኤርትራ ውስጥ ሻዕቢያ በሞኖፖል የያዘውን፣ "ቀይ ባህር የንግድ ኮርፖሬሽን" የተሰኘ ኩባንያን በበላይነት የሚመሩ ናቸው፡፡ ኩባንያው ከኤርትራ ሰማይ ስር የማይነግደው ነገር የለም፡፡ የሀገሪቱ ወጪና ገቢ፣ የባንክ፣ የቤት፣ የግብርና እና የማዕድን ንግዶች በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ለኤርትራ ህዝብ ዕለታዊ ፍጆታ የሚሆን ምግብም በህብረት ሱቆች አማካኝነት እያቀረበ ህዝቡን ይበዘብዛል፡፡ ከህዝቡ ካዝና የተመነተፈው ገንዘብም አቶ ኢሳያስ አስመራ ውስጥ ሰብስበው ለሚቀልቧቸው የክፍለ-አህጉሩ

አሸባሪዎችና ፀረ-ሰላም ኃይሎች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ይውላል። በአንፃሩ ደግሞ ነገሩ "ከመሞት መሰንበት" እንዲሉት ነውና፣ ምስኪኑ የኤርትራ ህዝብ ሻዕቢያ ህብረት ሱቆቸ ደጃፍ ተሰልፎ የዕለት ጉርሱን በወረፋ ይማትራል። በለስ ካልቀናውም ባዶ እጁን ወደ ቤቱ ይሄዳል።...ውጥንቅጡ በወጣ በኑሮ አዙሪት ቀለበት ውስጥ እየተንከላወሰ።...

ወንድም የሆነውን የሀገረ-ኤርትራ ህዝብ ለዚህ ሁሉ ስቃይ የተዳረገው አምባገነኑ የአስመራው መንግስት በሚከተለው የትርምስ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው። የዛሬ ዓመት ገደማ የወጣ የኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ ሪፖርት እንደሚያመለክተው፤ ኤርትራ በከፍተኛ የኢኮኖሚ አዘቅትና የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቃለች፡፡ አሁን ያለው ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ በሀገሪቱ አስከፊ አደጋ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ሁሉም ልማታዊ ሥራዎች በመንግስት ቁጥጥር ስር በመግባታቸው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ መሄዱን የሚገልጸው የድርጅቱ ሪፖርት፤ ሁኔታው በመላው ኤርትራ ላለፉት 11 ዓመታት የዘለቀና የተረጋጋ መስሎ ቢቆይም፣ ችግሩ በአቶ ኢሳያስ አገዛዝ ተዳፍኖ የነበረ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ለልማትና ሀገር ግንባታ እየተባለ በሰበብ አስባቡ በኃይል እየተተገበረ የሚገኘው የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ለሀገሪቱ ውድቀት መፋጠን ምክንያት መሆኑም ሪፖርቱ አክሎ ገልጿል፡፡ እንደ ድርጅቱ የፖለቲካ ተንታኝ ማርክ ሽናይደር ገለጻ፤ የተረጋጋ ይመስል የነበረው የኤርትራ አምባገነናዊ አገዛዝ ባጋጠመው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ በሂደት በመፈረካከስ ላይ ነው፡፡ አቶ ኢሳያስ ግን ይህን ችግር ከመጤፍ ባለመቁጠር ህዝቡን እያስራቡት አሸባሪዎችን በመመልመል፣ በማሰልጠን፣ በማደራጀትና በማስታጠቅና ለግብረ-ሽበራ የማሰማራት ተግባር ላይ ተጠምደው ቆይተዋል–ምንም እንኳን እያማራቸው ቢቀርም።....ግና እስቲ ጥቂቶቹን እኩይ ሴራቸውን ላስታውሳችሁ።...

አዎ ! 'ከአሸባሪነት የሚለየኝ ሞት ነው' ብሎ በቀረበው በአቶ ኢሳያስ መንግስት አቀነባባሪነት 16ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔን በማደናቀፍ አደጋ ለማድረስ የታቀደው አንዱ የከሸፈ ሴራ ነበር፡፡ በወቅቱ በጅቡቲ በኩል ሲ-4 የተሰኘ ልቁጥ ፈንጂን ከነማቀጣጠያው ይዘው የገቡት የአሸባሪው ኦነግ ተጠርጣሪ አባላት የተላኩትን የሽብር መልዕክት ሳያደርሱ በህዝቡ የነቃ ክትትልና በፀጥታ ኃይሎች የጋራ ጥረት በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ የኦነግ ቅጥረኞችና የተባባሪዎቻቸው ፈንጂውን የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ከመካሄዱም በፊት ጥቅም ላይ በማዋል ጉባዔው እንዲቋረጥ ዓላማ የነበራቸው ይሁን እንጂ፤ ይህ ከንቱ ምኞታቸው ቅዠት ሆኖ ቀርቷል– በጥብቅ የፀጥታ ማስጠበቅ ክትትል አማካኝነት፡፡እናም የምስራቅ አፍሪካው አዋኪ የላኳቸው አሸባሪዎች የመጀመሪያው ዕቅዳቸው ሊሰምር ባለመቻሉ፣ የስብሰባውን መጠናቀቅ በሁለተኛ አማራጭ ዕቅድነት ይዘው የሽብር ተግባሩን ለማካሄድ ሲንቀሳቀሱ አዲስ አበባ ውስጥ እጅ ከፍንጅ ሊያዙ ችለዋል፡፡

አሸባሪዎቹ የያዙት ፈንጂም በዓለም ዋንጫ ወቅት ኡጋንዳ ውስጥ ከፈነዳው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ መገኘቱም የሻዕቢያን ምስራቅ አፍሪካዊ የሽብር ተልዕኮን የሚያመላክት ነው፡፡ መቼም ውድ አንባቢዎቼ ከ76 በላይ የሚሆኑ ንጹሓንን ደም ያፈሰሰውን የኡጋንዳውን የፈንጂ ጥቃት አል -ሸባብ የተባለውና በአቶ ኢሳያስ የሚታገዘው የሶማሊያ ፅንፈኛ የአሸባሪዎች ስብስብ ኃላፊነት መውሰዱን ታስታውሳላችሁ፡፡ ታዲያ ለዚህ የሽብር ቡድን መሣሪያና ሌሎች ቁሳቁሶችን የሚያቀባብሉት የአስመራው የሽብርተኞች ቁንጮ ኢሳያስ አፈወርቂ መሆናቸውን ዓለም-ተገንዝቦት ሁለት ማዕቀቦችን ከጣለባቸውም ሰነባብቷል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን፣ የአስመራው የነውጥ ቡድን አልሞት የነበረው የሽብር ቀቢፀ-ተስፋ ከንቱ መፍጨርጨር ሆኖ ሳይሰምር ቀርቷል፡ ፡

እርግጥ እዚህ ላይ 'ህዝቡ በኑሮ ችጋር የሚመታበትን ሀገር የሚያስዳድሩት እንዲሁም የዘቀጠ ኢኮኖሚን የሚመሩት አቶ ኢሳያስ ከየት በመጣ ገንዘብ ነው ለሽርብተኞች ድጋፍ የሚያደርጉት?' የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ነገሩ ግን በሁለት መንገድ የሚታይ ነው። አንድም ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ከህዝቡ ካዝና የተመነተፈ ገንዘብ /ከቢሻ የወርቅ ማዕድንና ውጭ ከሚገኙ ኤርትራዊያን የሚሰበስቡት የሁለት በመቶ ቀረጥ/ ሲሆን፣ ሁለትም የአስመራው ቡድን የሚከተለው "የጦርነት ኢኮኖሚ ፍልስፍና" ነው። ታዲያ ይህ የሻዕቢያ አስገራሚ የኢኮኖሚ ፍልስፍና በኤርትራ የአሜሪካ አምባሳደር በነበሩት ግለሰብ ለሀገራቸው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በምስጢር በላኩት ሪፖርት አማኝነት ተረጋግጧል–ዊኪሊክስ የተሰኘው የመረጃ መረብ ምስጢራዊ መረጃውን ይፋ እንዳደረገው። ነገሩም ወዲህ ነው።…

…ይህ ፍልስፍና ሻዕቢያ ጦርነትን በመፍጠርና በማቀጣጠል፣ ከሂደቱ በተለያዩ መንገዶች ጥገኛ ካዝናውን የሚሞላበት አካሄድ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ለሽብርተኛው "ኦብነግ" እየሰጠ ያለው የስልጠና፣ የመሣሪያ አቀባባይነትና የደጋፊነት ሚና የዚሁ "የጦርነት ኢኮኖሚው" መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ ይኸውም ሻዕቢያ የሽብር ተግባርን ከሚደግፉና የኢትዮጵያን መናጋት ከሚሹ አንዳንድ የውጭ ሃይሎች ገንዘብ እየተቀበለ የሽብር ቡድኑን ያሰለጥናል፣ የሚላክለትን ሽብር መፍጠሪያ መሣሪያዎች ያቀብላል እንዲሁም የተለያዩ ሎጀስቲክሳዊ ድጋፎችን በማድረግ ኢትዮጵያ ሰላም እንዳትሆን ይሰራል፡፡ በዚህም ጦርነትን እንደ ንግድ ስራ በመቁጠር፣ በንጹሓን ደም ኪራይ መሰብሰቢያ ካዝናውን ይሞላል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም። ውስጣዊ ቀውስ የሌለባቸው የጎረቤት ሀገሮችን ፀረ - ሠላም ኃይሎች በአምሳያው ጠፍጥፎ እየሰራ ለሽብር ሥራ ይጠቀምባቸዋል፡፡ ይህን የሽብር ተግባሩን ከሚደግፉ ኃይሎች

“ኮሚሽን” (ለጉዳይ ፈጻሚነት የሚቆረጥ ክፍያ ማለት ነው) በመቀበል ኮሮጀው ባዶ እንዳይሆን ሌት ተቀን ይተጋል–ጠብ የሚል ነገር አላስገኘም እንጂ።

እርግጥም ምስጢራዊ መረጃው ይህ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር “የጦርነት ኢኮኖሚ ፍልስፍና” እየከሰረ መሆኑን እንዲህ ያስረዳል፡፡… አሁን ካለው የኤርትራ ህዝብ ግማሽ የሚሆነው ከነጻነት በኋላ የተወለደ እንደመሆኑ መጠን፤ በተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንጂ የቀድሞው የኢሳያስ አፈወርቂ የትግል ታሪክ እየተነገረው የሚኖር አይደለም፡፡ የዛሬው የኤርትራ ወጣት ትውልድ፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ምንዳ እየተሰጠው የጊዜ ገደብ በሌለው የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት የተነሳ ተስፋ አልባ መፃዒ ጊዜ ተጋርጦበት ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን ለወጣቱ እየተነገረ ያለውና የተሻለ መፃዒ ጊዜን በማለም አንድ ትውልድን የቀጠፈው የነፃነት ትግል ራዕይ የነበረው ቢሆንም፤ አቶ ኢሳያስ እየተከተሉ ባሉት “የጦርነት ኢኮኖሚ” ስሌት የሀገሪቱ የተስፋ ጎተራ በእጅጉ እንዲሟጠጥ ማድረጉን ያትታል፡፡…

ያም ሆነ ይህ ግን ማንኛውም ሰው ይህን የአቶ ኢሳያስ ተግባር ከማንነታቸው አንፃር መዝኖ ላይገርመው ይችላል። ግና ዳቦ ከናፈቀው ህዝብ መንትፎ አሸባሪዎችን የመርዳት አባዜ ከቶ ምን ይሉት የኢኮኖሚ መርህ እንደሆነ ከአቶ ኢሳያስ በስተቀር ለማንም ግልፅ እንደማይሆን መገንዘቡ አይቀርም።…እውነትም ከራስ ህዝብ ጉሮሮ ላይ ነጥቆ ለሽብር ተግባር ማዋል ምን ይሉት ጨካኔ ይሆን?…እርግጥ የዚህን ጥያቄ መልስ ለሁሉም ኤርትራዊ ዜጋ ብተወው የተሻለ ይመስለኛል–መፍትሔው ያለው እርሱ ጋ ነውና!

## ውሸትን እንደ መርህ

በኤርትራ መንግስት ውስጥ ውሸት አንድን እኩይ ሴራ ወይም ስትራቴጂ ለማሳካት የሚከናወን ስልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ዕውነታ ወደ አቶ ኢሳያስ አስተዳደር ሲመነዘር፣ ሰውዬው በሚናገሩት ነገሮች ውስጥ መዋሸት ብቻ ሳይሆን የተናወጠ እሳቤን ተመርኩዘው የሚያሰቡ መሆናቸውን ደግመው ደጋግመው ያስመሰከሩበት መርህ መሆኑን በተግባር አሳይተዋል፡፡ እርግጥ የኤርትራው አምባገነን ቡድን ውስጥ ውሸት በመርህ ደረጃ “እውነት” ነው፡፡ የአምባገነኑን ቡድን የማደናገሪያ ሃሳቦች እስካሳካ ድረስ፤ “እውነት ብትቀጥንም፣ አትበጠስም” የሚለው ሀገራዊ አባባል አይሰራም– በተገላቢጦሹ “እውነትን አቅጥነህና አመንምነህ በጣጥሰህ ጣላት” የሚለው የአስመራዊና የምዕዋዊ ቤተ- መንግስቶች አሳፋሪ ይትብሃል ነው ገቢራዊ የሚሆነው፡፡

ስለ ኤርትራ መንግስት የውሸት መርህ ሳወሳ በአንድ ወቅት አቶ ኢሳያስ የኳታሩ አል-ዋጣን ጋዜጠኛ የሆነውን አህመድ አሊን አስመራ ድረስ ጠርተው እንዴት እንደ ዋሹት ለአፍታ አስታወስኩ።…ነገሩ እንዲህ ነበር።…በወቅቱ ሻዕቢያ የሚመራበትን የውሸት መርህ ያላወቀው

ጋዜጠኛ አህመድ፤ "…ኧረ እባክዎ! ምን ነካዎት?! ታዲያ የኳታሩ ልዑል ሃሚድ ቢን ጃስሚን ባለፈው ዓመት ሰኔ ወር ላይ የሸመገሏችሁ ነገር ምንድነው?… ልዑሉ በይፋ እኮ ነው ስምምነቱን የገለጹት" በማለት የኤርትራው ሰራዊት "አሸዋ ለማምጣት" በሚል ሰበብ በሃይል ከወረረው ከጅቡቲው የራስ ዱሜራ ኮረብታዎች እንዴት እንደወጣ ይጠይቃል–ኢሳያስ አፈወርቂን ዓይን ዓይናቸውን እያየ፡፡ የምናውቃቸው አምባገነኑ ኢሳያስም ትላንት የለበሱትንም ጭምብል አውልቀው፣ በሌላ ጭምብል ዓይናቸውን በጨው ታጥበው እያጉረጠረጡ "…ትሰማኛለህ?! በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰጠ መግለጫም ሆነ ማስታወቂያ የለም፤ …ምንም ዓይነት ግጭት አልነበረም ስትባል፤ አልነበረም ማለት ነው፡፡ አይገባህም እንዴ?!…"አሉ፡፡ በጉዳዩ ላይ የተስማሙበትንና ዓለም ያወቀውን የአደባባይ ምስጢር ብሎም ለማፅቀብ የዳረጋቸውን አንደኛ ጉዳይ ሽምጥጥ አድርገው መካዳቸው ነው– ውሸትን እንደ መርህ የሚጠቀሙት የአስመራው "ነውጤ"፡፡…

…ይህን የውሸት መርህ አንባቢዎቼ ይበልጥ ትገነዘቡት ዘንድ ሰውዬው ጋዜጠኛ አህመድ ላነሳላቸው ጥቂት ጥያቄዎች የሰጡትን አስቂኝ ምላሾችን በመጠኑ ላስቃኛችሁ።…

***ጥያቄ፡-*** የኤርትራ ሠራዊት በኃይል ተቆጣጥሯቸው የነበሩትን የጅቡቲን ቦታዎች ለቆ እንዲወጣ አልተደረገም ነው የሚሉት?

***አቶ ኢሳያስ፡-*** እኛ ሠራዊታችንን ያስፈርንበት ቦታ የለም፡፡ የለቀቅነውም ግዛት የለም፡፡

***ጥያቄ፡-*** እየጠየኩዎት ያለሁት በጅቡቲ ግዛት ውስጥ የሚገኘውን የራስ ዱሜራ አከባቢን ነው እኮ?

***አቶ ኢሳያስ፡-*** በኤርትራና በጅቡቲ መካከል ምንም ዓይነት አወዛጋቢ መሬት የለም፣ አልነበረምም፡፡ የተያዘም፣ የተለቀቀም መሬት ፈጽሞ የለም፡፡

***ጥያቄ፡-*** የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በድንበር ውዝግቡ ዙሪያ መግለጫ አውጥቷል እኮ?

***አቶ ኢሳያስ፡-*** እውነትህን ነው? …እንዴት ነው ነገሩ? የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሌለ ነገር ላይ ምርመራ ሳያደርግ መግለጫ ያወጣል እንዴ? እንዴት ነው እንዲህ ዓይነት ነገር ሊሆን የሚችለው?

መቼም ውድ አንባቢዎቼ በቃለ-ምልልሱ “አቤት የውሸት መዓት” ማለታችሁ አይቀርም፡፡ አዎ! እንግዲህ የኤርትራው መሪ ማለት ይኸው ናቸው– እርሳቸውም ሆኑ መንግስታቸው እውነትን ተናግረው አያውቁም፡፡ እርሳቸው በለየለት “ዓይኔን ግንባር ያድርገው” የማደናገሪያ ብሂል ይህን ይበሉ እንጂ፤ እውነታው ሲገለጥ ግን ነገሩ እንዲህ ነው፡፡…በወቅቱ በኳታር መንግስት አደራዳሪነት በተካሄደው የኤርትራና የጅቡቲ መንግስታት ድርድር፣ ሻዕቢያ ከራስ ዱሜራ ኮረብታዎች ወታደሮቹን በቅሌት እንዲያስወጣ ተደርጓል፡፡ ወራሪነቱን አምኖም ለጁቡቲ የደም ካሳ ለመክፈልም ተስማምቷል፡፡

ምንም እንኳን አቶ ኢሳያስ ለጋዜጠኛው “…የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሌለ ነገር ላይ ምርመራ ሳያደርግ መግለጫ ያወጣል እንዴ?…” በማለት የትናንቱን እንደማያስታውስ ሰው ዓይነት ሆነው ምላሽ ቢሰጡም፤ በወቅቱ የመንግስታቱ ድርጅት ሻዕቢያ የጅቡቲን ግዛት በኃይል መውረሩን በራሱ አጣሪ ቡድን አማካኝነት አረጋግጧል፡፡ የማጣራት ሂደቱን ተከትሎም፣ ኢጋድ፣ አፍሪካ ህብረትና አረብ ሊግ ለምነዋል፣ አስለምነዋል፡፡ በምላሹ ግን የአስመራው ነውጠኛ ቡድን “በኤርትራና በጅቡቲ መካከል የድንበር ችግር መኖሩን አናውቅም” አለ፡፡ ይህን የኤርትራን መንግስት የጀብደኝነት አቋም የተረዳው የመንግስታቱ ድርጅትም፣ በጸጥታው ምክር ቤት አማካኝነት በውሳኔ ቁጥር 1862፣ የኤርትራ መንግስት ከጅቡቲ ግዛት በአስቸኳይ እንዲወጣ የሚያሳስብ መግለጫ አወጣ፡፡

… ይሁን ሁሉ ጥረት “ጆሮ ዳባ ልበስ” ያለው የአስመራው አምባገነናዊ አስተዳደር፣ ኤርትራን ከችግር ውስጥ ለማውጣት ተብሎ በኳታር መንግስት በቀረበው የስምምነት ውል መሰረት፣ በራሱ ጊዜ የቅሌት ካባውን ተከናንቦ የራስ ዱሜራን ኮረብታዎች ለኳታር ወታደሮች አስረክቦ በገባበት እግሩ ውልቅ ብሎ ወጥቷል፡፡

እርግጥ እዚህ ላይ አንባቢዎቼ “እውነታው ይህ መሆኑን ዓለም እያወቀው አቶ ኢሳያስ ለምን ይዋሻሉ?” የሚል ጥያቄ ልታነሱ ትችላላችሁ፡፡ አዎ! ጥያቄያችሁ አግባብ ያለውና ትክክለኛ ነው፡፡ ምንም እንኳን በወቅቱ የኳታሩ ጋዜጠኛ የአቶ ኢሳያስን ውሸት “…የተለመደ እና የእብድ ምላሽ” ቢለውም፤ እኔ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ግን በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡ የፖለቲካ ተንታኞችን ሃሳብም በተጨማሪነት ይጋራል፡፡ ይኼውም በዚያን ወቅት “የአስመራው መንግስት የጅቡቲን ግዛት በኃይል ይዞ አልለቅም ብሏል” የሚሉ ዓለም አቀፍ ዘገባዎችን ለማስተባበል የተደረገ የአፀፋ ምላሽ ነው፡፡ በዚህም አቶ ኢሳያስ በወራሪነታቸው “የለመደች ጦጣ …” እንዳይባሉ “የያዝነውም ሆነ የለቀቅነው ቦታ የለም” በማለት ከራስ ዱሜራ ኮረብታዎች በቅሌት አለመውጣታቸውን ለማስተባበል መሞከራቸው ነው– ይህ ቀሽም የፖለቲካ ድራማ ማዕቀብ እንዲጣልባቸው ከማድረግ በስተቀር ጠብ የሚል ነገር ባያስገኝላቸውም፡፡…

በአጠቃላይ የኤርትራ መንግስት ኦብነግን የመሳሰሉ አሸባሪዎች ግብረ-ሽበራን እንዲፈፅሙ ሁሉን አቀፍ እኩይ ድጋፍና እገዛ እያደረገ መልሶ “ዓይኔን ግንባር ያድርገው” እያለ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ የሚዋሽ ቡድን ነው። ይህ በመንግስትነት ተደራጅቶ ሁሉንም ነገር እንደ መንደር ዱርዬ በስብቀት ለመሸፋፈን የሚሞክረው የአስመራው ቡድን ከዚህ አኳያ በሚከውነው አስቂኝ ተግባር እያሞኘ ያለው ራሱን ብቻ ነው—ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሁሉንም ነገር አውቆበታልና። እናም የሚሰማው የሌለ መሆኑን መረዳት ይኖርበታል ባይ ነኝ። ዳሩ ግን ይህ የውሸት መርሁ ደሙ ውስጥ ያለ በመሆኑ ሊተወው አይችልም። ሌላው ቀርቶ ሻዕቢያ ከህዝቡ ካዝና መንትፎ ሰሞኑን አስመራ ውስጥ ለአሸባሪው “ኦብነግ” ጉባኤ ማካሄጃ ያወጣውን ገንዘብ በተመለከተ የኳታሩ ጋዜጠኛ ተመልሶ በምናብ ቢጠይቃቸው፤ “…ማን? እኛ? መቼና የት ነው እንዲህ ያደረግነው?” ብሎ ከማደናገር አይመለስም—ቅጥፈትን እንደ የወንበሩ ዕድሜ ማራዘሚያ መድሃኒት አድርጎ እየተጠቀመበት ነውና። አበቃሁ።